https://www.path-2-happiness.com/am

ሲገልጽም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱلسَّمَآءَ بَنَيْنَـٰهَا بِأَيْيْدٍ وَإِنَّا لَمُوسِعُونَ ﴿٤٧﴾} [الذاريات: ٤٧]،

‹‹ሰማይንም በኃይል ገነባናት፤እኛም በእርግጥ [ለማስፋት] ቻዮች ነን::››[አል ዛሪያት:47]

ፀሐይ በራሷ ምሕዋር የምትጓዝ መሆኑን ሲገልጽ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَءَايَةٌ لَّهُمُ ٱلَّيْلُ نَسْلَخُ مِنْهُ ٱلنَّهَارَ فَإِذَا هُم مُّظْلِمُونَ ﴿٣٧﴾ وَٱلشَّمْسُ تَجْرِى لِمُسْتَقَرٍّ لَّهَا ۚ ذَٰلِكَ تَقْدِيرُ ٱلْعَزِيزِ ٱلْعَلِيمِ ﴿٣٨﴾} [يس: ٣٧- ٣٨].

‹ሌሊቱም ለነሱ ምልክት ነው፤ከርሱ ላይ ቀንን እንገፍፋለን፣ወዲያውኑም እነሱ በጨለማ ውስጥ ይገባሉ:: ፀሐይም ለርሷ ወደ ኾነው መርጊያ ትሮጣለች፤ይህ የአሸናፊው፣የዐዋቂው፣አምላክ ውሳኔ ነው::››[ያሲን:37]

የነቢዩ ሱንናም ከዚህ ተአምር የራቀ አይደለም:: ከእመ ምእመናን ዓእሻ (ረ.ዐ.) በተላለፈው መሰረት፣የአላህ መልክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፦ ‹‹ እያንዳንዱ የኣደም ልጅ ሦስት መቶ ስልሳ የአጥንት መገጣጠሚያዎች ይዞ ነው የተፈጠረው፤በነዚያ ሦስት መቶ ስልሳ አጥንቶች ቁጥር፣‹አልሏሁ አክበር›፣አልሐምዱ ሊልላህ›፣‹ላእላሀ እልላልሏህ›፣‹ሱብሓነልሏህ› እና ‹አስተግፍሩልሏህ› ያለ ሰው፣ሰዎች ከሚሄዱበት መንገድ ላይ ድንጋይ ወይም እሾህ፣ወይም አጥንት ያስወገደ፣በበጎ ነገር ያዘዘ፣ወይም ከክፉ ነገር የከለከለ ሰው በዚያ ዕለት ራሱን ከእሳት ያረቀ ሆኖ ይውላል::››[በሙስሊም የተዘገበ]

ዛሬ በሳይንስ እንደ ተረጋገጠው የሰው ልጅ እነዚህ አጥንቶችና መገጣጠሚያዎች ባይኖሩት ኖሮ፣ሕይወቱን መምራትና ኑሮን ማጣጣምም ሆነ የተጣለበትን በምድር ላይ የምትክነት ተልእኮ መወጣት ባልቻለ ነበር:: ከዚህ ስንነሳም የፈጣሪን ታላቅ ጥበብና ድንቅ ውሳኔ ለሚመሰክረው ለዚህ ትልቅ ጸጋ የሰው ልጅ በየቀኑ ምስጋና የማድረስ ግዴታ ይኖርበታል:: በዚህ ሐዲስ ውስጥ ተአምራዊው ነገር ነቢዩ ﷺ እንዲህ ዓይነቱ ዕውቀት የትምና ማንም ዘንድ ባልነበረበት ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንዲህ በረቀቀ ሁኔታ የሰው አጥንት መገጣጠሚያዎችን መግለጻቸው ነው:: እንኳ በዚያ ዘመን ዛሬ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን አብዛኛው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ብዙ የሕክምና ሳይንስ መምሕራን ጭምር ይህን አያውቅም!! ዛሬ ዘመናዊው ሳይንስ ልክ ነቢዩ ﷺ ከአስራ አራት ክፍለ ዘመናት በፊት እንደተናገሩት ባረጋገጠው መሰረት፣በሰው አካል ውስጥ ሦስት መቶ ስልሳ የአጥንት መገጣጠሚያዎች ይገኛሉ:: 147ቱ በጀርባ አከርካሪ አጥንት ሲገኙ፣24ቱ በደረት፣86ቱ ከወገብ በላይ ባለው ክፍል፣88ቱ ከወገብ በታች ባለው የሰውነት ክፍል፣15ቱ ደግሞ በዳሌ ገንዳ ይገኛሉ::

እዚህ ላይ የግድ መነሳት ያለበት ጥያቄ ፦ ከፈጣሪው አላህ (ሱ.ወ.) በስተቀር ይህንን የሰው ልጅ ዕውቀት በሃያኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻዎች ላይ እንጅ ያልደረሰበትን ልዩ የሆነ ሳይንሳዊና ሙያዊ እውነታ ለነቢያትና ለመልክተኞች መደምደሚያ ﷺ ማን ሊያስተምር ይችላል?! የሚለው ነው::



ነቢዩን ﷺ ከሰው ግንዛቤ በላይ የሆነውን እንዲህ ያለውን ጉዳይ እንዲያነሱ ሊያደርጋቸው የሚችለውስ ማን ሊሆን ይችላል?! አላህ (ሱ.ወ.) በገደብ የለሽ ዕውቀቱ የሰው ልጅ አንድ ቀን በዚህ የአቶኖሚ ግኝት ላይ ሊደርስ እንደሚችል ስለሚውቅም ነቢዩን ﷺ አሳውቋቸዋል:: ከዚህ ነቢያዊ ሐዲሥ የሚንጸባረቀው የሐቅ ብርሃን ለእኚህ የመልክተኞች መደምደሚያ ነቢይ እውነተኛነትና ከመለኮታዊ ራእይ ጋር ስላላቸው ትስስር እርግጠኝነት የጸና ማስረጃ ነው::

የሳይንስና የስልጣኔ መንገድ ግን የመልካም ስነምግባር መንገድ ካልሆነ፣ለሰው ልጆች ተድላና ደስታ የማያገለግል፣ለጥፋትና ለዕድለ ቢስነት የሚያጋልጣቸው የመከራና የዋይታ አጥፊ ስልጣኔና አውዳሚ ዕውቀት እንጂ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም! ስለዚህም የስልጣኔና የዕውቀት መንገድ የመልካም ስነምግባርና የሞራላዊ እሴቶች መንገድም ጭምር ነው:: ዕውቀትና ስልጣኔ የሌለበት የደስተኝነትና የመታደል መንገድ ቅዥትና ከንቱ ተረት እንደሆነ ሁሉ፣መከመልካም ስነምግባርና ከሞራላዊ እሴት የተራቆተ የዕውቀትና የስልጣኔ መንገድም ግለሰቦችን፣ማህበረሰቦችንና መላውን የሰው ልጅ ለጥፋትና ለውድመት የሚያጋልጥ መንገድ ነው::



### የማያነብና የማይጽፍ መልክተኛ

‹‹እነዚያ አንቀጾች ከአንድ ማንበብና መጻፍ ከማይችል ሰው እንዴት ሊመነጩ እንደሚችሉ ለማወቅ አእምሮ ግራ ይጋባል:: መላው የምሥራቅ ሕዝብ በቃላቸውም ሆነ በይዘታቸው መሰሎቻቸውን የሰው ልጅ አእምሮ ማመንጨት የሚሳነው አንቀጾች መሆናቸውን አምኖ ይቀበላል::››

**ሄንሪ ዴ ካስትሬ**

**የፈረንሳይ ጦር ቀድሞ ሻምበል**



### የዩኒቨርስ ተአምራት

‹‹ያልተማረውና በማይማን አካባቢ ውስጥ ያደገው ሰው ሙሐመድ፣ቅዱስ ቁርኣን የገለጸቸውንና ዘመናዊው ሳይንስ እስከ ዛሬው ዘመናችን ድረስ ሊደርስባቸው የሚጥረውን የዩኒቨርስ ተአምራት እንዴት ማወቅ ቻለ?! እናም ይህ ንግግር የግድ የአላህ (ሱ.ወ.) ንግግር መሆን ይኖርበታል::››

**ዲዮ ሪፖርተር**

**በአሜሪካ የሚታተም ጋዜጣ**

